# ምን አዲስ ነገር አለ

VOTE 2026

## ሚኒሶታ የመምረጥ ነፃነትን የሚያስፋፉ አንዳንድ አዲስ ህጎች አሉዋት!

### የመምረጥ ችሎታን መመለስ

አሁን፣ እስር ቤት የለቀቁ የሚኒሶታ ነዋሪዎች በዲሞክራሲያችን ውስጥ ይካተታሉ። ማንኛውም የወንጀል መዝገብ በአሁኑ ጊዜ የከባድ ወንጀል ፍርድ በመስራት እስር ላይ ካልሆኑ በስተቀር ለመምረጥ ያልዎትን መብት አይነካም።

እስር ውስጥ ካልሆኑ፣ በፕሮቤሽን ወይም በይቅርታ ጊዜ ላይ ከሆኑ ወይም ካሳ የሚከፍሉ ከሆነ፣ ድምጽ ለመስጠት ብቁ ነዎት።

### ራስ-ሰር የመራጭ ምዝገባ

በ2024 ዓ.ም. ሚኒሶታ ራስ-ሰር የመራጭ ምዝገባ ታቋቁማለች። አንዴ ከተቋቋመ፣ ለአስተማሪ ፈቃድ፣ ለነጂ ፈቃድ ወይም ለስቴት መታወቂያ የሚያመለክቱ ሰዎች፣ ዜግነትን ጨምሮ ሁሉንም የብቃት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ ለመምረጥ ይመዘገባሉ።

ድምጽ መስጠትን ቀላል ከማድረግ በተጨማሪ፣ ይህ የምርጫ ባለሥልጣናት የመራጮችን መዝገብ የማዘመን ሂደቱን ለማቀላጠፍ ያስችላቸዋል።

የሚኒሶታ ነዋሪዎች ምዝገባቸው ከተካሄደ በኋላ በ20 ቀናት ውስጥ ለመምረጥ ከመመዝገብ መውጣት ይችላሉ።

### የ2026 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 11 ቀን

በአካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በአካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 18ቀን እስከ ህዳር 2 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 13 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 3 ቀን

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት
mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE

*...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ*

## ለ16 እና 17 አመት የሆኑ ቅድመ-ምዝገባ

አሁን፣ 16 እና 17 አመት የሆኑ የሚኒሶታ ነዋሪዎች የመራጭ ምዝገባ ቅጽ ማስገባት ይችላሉ፣ እና ምዝገባቸው በ18ኛ ልደታቸው ላይ ይፀናል። ሚኒሶታ ወጣቶችን በማሳተፍ ብሔራዊ መሪ ናት፣ እና ወጣት ሰዎች እራሳቸውን እንደ ወደፊት መራጮች እንዲያዩ ማድረግ የዚህ ትልቅ ክፍል ነው።

## ከቤት ተቀምጦ የመምረጥ ቀጣይነት

ብዙ የሚኒሶታ ነዋሪዎች በመራቅ ድምጽ መስጫ ወረቀት ከቤታቸው ተቀምጠው የመምረጥ ምቾትን ይደሰቱበታል። ማንኛውም ብቁ መራጭ በዚህ መንገድ ሊመርጥ ይችላል፣ እና እ.ኤ.አ. ከሰኔ 2024 ጀምሮ ለእያንዳንዱ ምርጫ እንደገና ማመልከት ከመፈለግ ይልቅ በቅድሚያ የድምጽ መስጫ ዘመን ወቅት በራስ-ሰር የመራቅ ድምጽ መስጫ ወረቀት እንዲላክላቸው በዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ከቤት ተቀምጠው መምረጣቸውን መቀጠል የሚፈልጉ መራጮችን ጊዜ ይቆጥባል።

## የቋንቋ ድንጋጌዎች

ከጥር 2024 ጀምሮ፣ በመላ ሀገሪቱ በእያንዳንዱ መራጫ ቦታ በአጠቃላይ በተለመደ ሁኔታ ከእንግሊዝኛ ውጭ በሚነገሩ ሶስት ቋንቋዎች የመራጭ መመሪያዎች ይሰጣሉ። በሴንሰስ መረጃ መሰረት፣ ብቁ በሆኑ መራጫ ቦታዎች ተጨማሪ የቋንቋ ዕገዛ ይሰጣል።

- ቢያንስ 3% ሕዝብ እንግሊዝኛን “በጣም ደካማ” የሚናገሩ ከሆኑ፣ የተተረጎሙ የድምጽ መስጫ መመሪያዎችን እና የናሙና ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ያቀርባሉ።
- ቢያንስ 20% ሕዝብ እንግሊዝኛን “በጣም ደካማ” የሚናገሩ ከሆኑ፣ ሲጠየቁ፣ በምርጫ ቀን በሚገኙበት ምርጫ ክልል የትርጉም አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። መራጮች ደግሞ ከምርጫ ክልላቸው ብቁ የሆኑ ቢያንስ 10 ፊርማዎችን ያካተተ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።